ቢስሚላሂ አረህማን አረሂም

# የበድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ፌዴሬሽን አመታዊ ጉባኤ የመክፈቻ እለት ዝግጅት አስመልክቶ የተዘጋጀ ዘገባ

ሙሀባ ጀማል
ሳዲቅ አህመድ

አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱ

ዛሬ ጁላይ 26 2007 በአትላንታ የነጃሺ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ማህበር አስተናጋጅነት የተጀመረውን የበድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ፌዴሬሽን አመታዊ ጉባኤን ለመሳተፍ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሙች በአሜሪካ በካናዳና አውሮፓ ከሚገኙ የተላያዩ ግዛቶች ወደ አትላንታ መምጣት የጀመሩት ገና የምሽቱ ጨለማ ለቀኑ ብርሃን እጅ ሳይሰጥ ነበር። ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ታዳሚዎች በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው የመጡ ቢሆንም ፊታቸው ላይ የድካም ሳይሆን የደስታና የጉጉት ስሜት ነበር የሚንጸባረቀው። ለረጂም ጊዜ ያልተገናኙ በሳቅና በደስታ ሲተቃቀፉና አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱ እየተባባሉ በጋለ መንፈስ እስላማዊ ሰላምታን ሲለዋወጡ፣ ህፃናትና ወጣቶች በደስታ ሲፈነድቁ መመልከት ለልብ ደስታን ለአይን ደግሞ እርካታን ያጎናፅፍ ነበር። ሰአቱ ከቀኑ አስራሁለት ሲሁን ጉባኤው የተዘጋጀበት እስከ አሁን ድረስ የበድር አመታዊ ጉባኤዎች ከተሄዱባቸው ቦታዎች በመሉ በትልቀቱ ወደር እንደሌለው የተነገረለት የክራውን ፓላዛ ሆቴል ሂጃብ በለበሱ ኢትዮጵያውያን ሙስሊም እህቶች፣ ፊቶቻቸው በፈገግታ በተሞላ ወንድሞችና በበርካታ መቶዎች የሚቆጠሩ ታዳጊ ህጻናት ተጨናንቆ ነበር።

ሰው መምጣቱን በጊዜ ባለማብቃቱ ጉባኤው የተጀመረው ከታቀደለት ጊዜ ከአንድ ሰአት በላይ ዘግይቶ ነበር። ታዳሚው በፕሮግራሙ መዘግየት ሳይበሳጭ በትእግስትና በነሻጣ ሲጠባበቅ ቆይቶ ሰአቱ ልክ ከምሽቱ ሰባት ፒ.ኤም. ሲሆን በቁርአን ተከፈተ። ይህንን በናፍቆትና በጉጉት ሲጠበቅ

የነበረውን ጉባኤ በቁርአን የከፈተው የትላንታው ወጣት መሃመድ አወል አብዱልወሃብ ነበር። በመቀጠልም የአትላንታ ሙስሊሞች መሪ የሆኑት ሸህ አወል አሊ አብዱልወሃብ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር አደረጉ። ሸህ አወል በንግግራቸው ላይ የበድርን ጉባኤ ከሌሎች የስብሰባ አይነቶች የሚለየው የስብሰባው አላማ ዲነል ኢስላምን የሚመለከት መሆኑና ትርፍ እንጂ ኪሳራ የሌለው መሆኑ እንደሆነ ገልጸው ኢትዮጵያዊው ሙስሊም በገዛ ሃገሩ እያለ እንደሌለ ለማድረግ የሚደረገውን ልማድ ለማስወገድና ሁለንተናዊ መለዮውን ለማጉላት ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ ሙስሊሙ መነሳት እንዳለበት አሳስበዋል።

በመቀጠል መድረኩን የተረከቡት የአትላንታ ህጻናት ሲሆኑ የጉባኤውን ተሳታፊዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እንኳን በደህና መጣችሁ ሲሉ ታዳሚዎች ደስታቸውን በተክቢራ አሰምተዋል። ህጻናቱ ዝግጅታቸውን እንዳጠናቀቁ የበድር ቦርድ ሰብሳቢና የካናዳ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መሪ የሆኑት ሸህ መሃመድ አወል መድረኩን በመረከብ በድር በያዝነው አመት ያከናወናቸውን አበይት ተግባራት ለተሰብሳቢው ገልጸዋል። በገለጻቸውም ላይ በድር በያዝነው አመት ካከናወናቸው ተግባራት ሁሉ ዋነኛው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ያጸደቀው የሃይማኖት ነጻነት ተግባራዊ እንዲሆን፣ የሙስሊሞች የእምነት ነጻነትና መብት እንዲከበር የኢትዮጵያ መንግስትን ለማሳሰብ ከአሜሪካ፣ ከካናዳ፣ ከአውሮፓና ከመካከለኛው ምስራቅ የተውጣጡ ዘጠኝ አባላት ያሉት አንድ የልኡካን ቡድን ፌዴሬሽኑ ወደ ኢትዮጵያ መላኩ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢስላማዊ መለዮ በምዕራቡ ዓለም በሚል ርዕስ ዙርያ የምዕራቡ ዓለም በሙስሊሙና በተለይም በልጆች አስተዳደግ ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመከላከል ምን መደረግ እንዳለበት ሰፋ ያሉ ማብራሪያዎችን የሰጡት ወንድም ረምዚ ሸሪፍና ሸህ አወል አሊ ሲሆኑ እነርሱም የተለያዩ የቁርአን አንቀጾችንና የነብዩ ሶአወ ሃዲሶች እያጣቀሱ ልብን የሚመስጡ ዳአዋዎችን አድርገዋል።

የደዓዋው ፕሮግራም ካበቃ በኋላ ሙሳፊሩ የመግሪብና የኢሻ ሰላትን አከታትሎ ሰግዶ እራትም ተበልቶ የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቋል።

July 26 2007
Atlanta, USA